ግንቦት 7
የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

Ginbot 7
Movement for Justice, Freedom and Democracy

# ለወያኔ የፍትህ ቧልት ቁብ የሚሰጥ ጆሮ ግንቦት 7 የለውም

## ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ

ቀን ነሐሴ 1 2001

የወያኔ ካድሬዎች በረት የሆነውና ራሱን ከፍተኛው ፍርድ ቤት ብሎ የሚጠራው ወራዳ ተቋም ሃምሌ 30 2001 ኢ.ም በነጀኔራል ተፈራ መዝገብ የተከሰሱ የግንቦት 7 መሪዎች በተከሰሱበት ክስ ወንጀለኞች ናቸው ብሏል፡፡ አያይዞም እነ ጀኔራል ተፈራ ማሞ በአቃቤ ህጉ ወንጀለኛነታቸውን የሚያመላክት በቂ ማስረጃ ስለቀረበባቸው ራሳቸውን ይከላከሉ ብሏል።

በርካታ ኢትዮጵያውያን፣ የአለም አቀፍ ማህበረሰቡና የመገናኛ ብዙሃኑ በእዚህ ብይን ላይ የግንቦት 7 ንቅናቄ አቋም ምን እንደሆነ ለማወቅ እንደሚሹ ለግንቦት7 ንቅናቄ ከሚደርሱት የተለያዩ መልእክቶች ማወቅ ችለናል፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ምላሽ አጭርና ቀላል ነው፡፡

ግንቦት 7 «የወያኔ አገዛዝ የ1997ቱን የህዝብ የምርጫ ውሳኔ በአመጽ ገልብጦ በመፈንቅለ ህዝብ ውሳኔ ስልጣን ላይ የተከመረ አገዛዝ ነው» ብሎ ያምናል ፡፡ በመሆኑም ይህን ህገወጥ አገዛዝና ይህ አገዛዝ ላቆማቸው ማናቸውም ተቋማት ግንቦት 7 እውቅና አይሰጥም፡፡ ይህ አቋማችንም የወያኔን የፖለቲካ ፍላጎት ከማስፈጸም ውጭ ሌላ የህልውና ምክንያት የሌላቸወን ፍርድ ቤቶችንና አጠቃላይ ወያኔ የፍትህ ተቋማት የሚላቸውን አካላት ያጠቃልላል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ፣ አመራሩ ስለተከሰሱበት ጉዳይና ስለተላለፈባቸው ብይን አስተያየት ለመስጠት፣ በቅድሚያ በኢትዮጵያችን ህጋዊ መንግስት መኖሩን፣ ነጻ የሆነ የፍትህ ስርአትና ህሊናቸውና ህግ ብቻ የሚያዛቸውን ተከትለው ውሳኔ የሚሰጡ ዳኞች ያሉበት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ የግድ ይላል የሚል አቋም አለው፡፡ ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያችን የለም፡፡

በኢትዮጵያችን ህግ ማለት የመለስ ዜናዊ ፍላጎት ብቻ ነው፡፡ ፍርድ ቤት የመለስ ዜናዊንና የዘረኛ ባልደረቦቹን ፍላጎት ማስፈጸሚያ፣ በዜጎች ላይ ሽብር መንዣ የአጋዚ ጦር መንትያ ወንድም ነው፡፡ በእንዲህ አይነቱ ሃገር ፍትሃዊ የሆነ የህግ ሂደት፣ ዳኝነት፣ ብይን የመሳሰሉት ቃላት ትርጉም የላቸውም፡፡ ለእዚህም ነው ግንቦት 7 የወያኔን የፍትህ ቧልት የሚያዳምጥበት ጆሮ የሌለው፡፡ ስለፍርድ ሂደቱና ውሳኔው በማውራት የወያኔ የቅጥፈት ድራማ አካል መሆን የማይፈልገው፡፡

በመጪው ነሃሴ 19 2001 ችሎትም የወያኔ ካድሬዎች ጀነራል ተፈራ ማሞንና ባልደረቦቹን፣ እንዲሁም ወይዘሮ እማዋይሽ አለሙና የ83 አመቱ አረጋዊ አቶ ጽጌ ሃብተማሪምን ጨምሮ፣ መፈንቅለ መንግስትና የወያኔን ከፍተኛ ባለስልጣናት ለመግደል ሙከራ ማድረጋቸው በአቃቤ ህጉ በመረጋገጡ ወንጀለኞች ናቸው የሚል የተለመደውንና ሃገሬ አይቀሬ የሚለውን ብይን እንደሚሰጡ ይጠበቃል፡፡ በእዚሁ እለት ደግሞ ለግንቦት 7 አመራር አካላትም የሞት ቅጣት በአቃቤ ህጉ አስጠይቆ፣ በካድሬ ዳኛዎቹ ሚዛናዊነት የተሻሻለ በሚመስል ብይን የእድሜ ይፍታህ ቅጣት እንደሚያስተላልፍ አሰቀድሞ ለማወቅ የአዲስ አበባን ባለውቃቢና ቃልቻ መቀለብ አያስፈልግም፡፡

እንዲህ አይነቱ ውሳኔ የሚተላለፈው ግን ወያኔ ማስረጃ በእጁ ስላለው፣ አቃቤ ህጉና ጠበቆች የሚሉትን ዳኞች በፍትሃዊነት መዝነው ብይን ሰለሚሰጡ አይደለም፡፡ ለፍርድ ቤቱ ታዳሚዎች የማይታየው፣ በመሃል ዳኛው አናት ላይ ምንጣፉን ዘርግቶ የተንዘራፈጠው መለስ ዜናዊ ስለፈለገው ብቻ ነው፡፡

በመለስ ዜናዊ አይን የግንቦት 7 መሪዎችና ከእዚህ ድርጅት ጋር ግንኙነት አላቻው ተብለው ወህኒ የተወረወሩት እነ ጀነራል ተፈራ ማሞ ወንጀለኛ የሆኑት ዘረኛነት፣ ዘረፋን፣ ሃገራዊ ክህደትን አጥብቀው ስለሚጠሉ ብቻ ነው፡፡

ውርደትን፣ ባርነትን አሜን ብለው ለመቀበል ፍላጎቱ ስለሌላቸው ብቻ ነው፡፡ ፍትህን፣ ነጻነትንና ዴሞክራሲን ከልባቸው ሰለሚወዱ ብቻ ነው፡፡

ይህ ወንጀል ከሆነ የግንቦት 7 መሪዎች ሽህ ግዜ ወንጀለኞች ነን ለማለት አይከብዳቸውም፡፡ ጄነራል ተፈራና ባልደረቦቹም እንደ ግንቦት 7 መሪዎች «ዘረኛነትን መጥላት፣ ሃገርን መውደድ፣ ለመብትና ለክብር መቆም፣ ወንጀለኛ የሚያደርገን ከሆነ አዎን ወንጀለኖች ነን» ለማለት ድፍረቱ ያላቸው ለመሆናቸው ግንቦት 7 ሙሉ እምነት አለው፡፡

የግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ